# ዶ/ር በያን አሶባ ለግልጽ ደብዳቤዬ ለሰጡት ምላሽ መልስ

## ውድ ዶ/ር በያን አሶባ

በቅርቡ ለጻፍኩልዎት ግልጽ ደብዳቤ የከተቡልኝን አጻፋ በኢትዮሜዲያ ድሕረገጽ አስፍረውት ዐየሁት፡፡ የደብዳቤዎን ርዕስ እንደ አጤንኩት "እኚህ ሰው በጣም ትልቅ ናቸው፣ ቢዘገዩም መልስ ሠጡኝ፡፡ እንግዲህ ስለሕዝባችን ዕጣ ፈንታ በቁም-ነገር ሊያነጋሩኝ ነው፣" በማለት አክብሬዎት ነበር፡፡ ወደ ውስጥ ዘልቄ ሳስተውለው ግን ለካስ እርስዎ የሕዝባችንን ሕይወት የሚነካውን አንገብጋቢ ቁም-ነገር ወደ ጎን ትተው የእርስዎንና የእኔን ስሞች አንስተው እየሰነጣጠቁ ኖሯል የከተቡልኝ፡፡ እኔም ሆንኩ የኢትዮሚዲያ አንባቢዎች እርስዎን ከሚያህል ትልቅ ሰው የጠበቅነው ይህን አልነበረም፡፡ ይህም በመሆኑ "እኒህ ሰው ለግል ስማቸውና ክብራቸው ነው የሚቆረቆሩት ወይንስ ለታላቁ የኦሮሞ ሕዝብ?" ስል ራሤን ጠየቅኩ፡፡

የሆነ ሆኖ ስምዎን አሳስቼ በመጻፌ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡ ስምዎን እንደዛ ብዬ የጻፍኩት እርስዎ እንዳሰቡት ሆነ ብዬ በፖለቲካዊ ምክንያት ወይም እርስዎን ባለማክበሬ ሳይሆን፣ ስምዎን ከዛ በፊት ሰምቼ ባለማወቄ ለጆሮዬ ባዕድ ስለ ነበር ነው፡፡ ስምዎን ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት ከሳምንታት በፊት በኢሳት ሬዲዮ ሲጠራ ነበር፡፡ እርስዎም ቢሆኑ የእኔን ደብዳቤ ከማየትዎ በፊት እኔን ያወቁኝ አይመስለኝም፡፡ የኢሳት ሬዲዮ አስተዋዋቂ ስምዎን ሲናገር ለጆሮዬ "በያና ሱባ" የሚል መስሎ ተሰማው፡፡ "ሱባ" በሚለው ቃል ኢትዮጵ ልጁን የጠራበት ከመሆኑም በላይ እኔ እስከማውቀው ድረስ በጥንት ኦሮሞዎች ዘንድ የተከበረ ስም በመሆኑ በእውነቱ ሥምዎ መሰለኝ፡፡ ስለ እዚህም "እኚህ ሰው የከበረ የጥንት የኦሮሞ ስም አላቸው፣ ስማቸውን ከሱባ ፊደላት ጋር አያይዤ ብናገር ይገጣጠማል፣" ብዬ ወደድኩት፡፡ የሚያሳዝነው፣ ለካስ ተሳስቼ ኖሯል! በቃ ነገሩ ይኼው ነው፡፡ የሚገርምዎት ነገር፣ "ሱባ" የተባለውን ለ 4000 ዓመታ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረውን የጥንት ስም እኔ እሩቅ ሄጄ ስፈልግ፣ ለርስዎ የጻፍኩልዎትን ደብዳቤ የ አነበቡ ጥቂት ሰዎች በ ስልክና በ ኢሜል፣ " ከአዲስ አበባ ወጣ ብለህ፣ ወደ ሆለታ መናገሻ ስታመራ፣ በስተግራ ተጠምዝዘህ ከሄድክ "ሱባ" የሚባል የኦሮሞ ሰፈር አለልህኮ፣" ብለው አበሰሩኝ፡፡ ምናልባት እርስዎ ይህን ቦታ ያውቁት ይሆናል፡፡ ከ 4000 ዓመታት በፊት ኢትዮጵ ለልጁ የሰየመው ስም አሁንም ድረስ መኖሩና በሆለታ አካባቢ የኦሮሞዎችን ቀዬ ስም ይዞ መገኘቱ የኦሮሞ ሕዝብ ከኢትዮጵ እና ከኢትዮጵያ ጋር አንድ ዐይነት ግንኙነት እንደ አላቸው ይመሰክራል፡፡ የጥንት ኦሮሞ ሊቃውንት በሱባ ቋንቋ ይጽፉ ነበር ያልክዎትም ከዚህ ጋር የተሰናሰለ ነው፡፡ የሱባ ፊደላት እና ከፊደላቱ በተጨማሪ የሱባ እና የግዕዝ መዝገበቃላት በድሮ ዘመን ተቀብረውበት በነበሩበት ስፍራ ከ 45 ዐመታት በፊት ስለተገኙ ስለ ሱባ ኢትዮጵያዊነትና ነባርነት የመረጃ ችግር የለም፡፡

ስምዎን አስመልክቶ፣ ሀቁ ይሄ እላይ የተጠቀሰው ሳለ፣ ክቡርነትዎ ግን ብዙ ብዙ ክፉ ነገሮች በቁጣ አተቱ፡፡ በስሜት ጎዳና እጅግ ርቀው ሄደውም መሪር ንግግሮችን ተናገሩ፡፡ የአንድ ብሄር ሰዎች ተሰብስበው በእርስዎ ላይ ሴራ ያሴሩም አስመሰሉ፡፡ ኢላማዎ እንድሆን በማይገባኝ በኔ ላይ የቃላት እሩምታ ተኮሱ፡፡ የእኔ ዐይነቱ አንድ ግለሰብ ስምዎን አሳስቶ ስለጻፈ ብቻ ተበሳጭተው ስለ ተለያይቶ መኖር አስፈራሩ፡፡ እኔም "እኚህ ሰው በቀደም እለት በኢሳት ሬዲዮ አብሮ ስለ መኖር አብስረው አልነበረም እንዴ? ከመቼው ሃሳባቸውን ለወጡ? የሃገር ጉዳይ እንዲህ በቀላሉ የሚለዋወጥ ነው እንዴ?" ብዬ ተደመምኩ፡፡

ከዚሁ እኩል እኔን ያሳዘነኝ ግን፣ እኔ በኢትዮጵያዊነቴ እና በኦሮሞነቴ እጅግ የምኮራ የኢትዮጵያ ኦሮሞ ሆኜ ሳለ እኔን እንደ በርካታ ሰዎች ቆጥረው ማንነቴን በድፍረት በመለወጥ "እናተ አበሾች" ብለው እኔ በአልሆንኩት በአበሻነት አለአግባብ ፈረጁኝ፡፡

"እሳቸው ለራሳቸው ስም እንዲያ እየተንገበገቡ እንዴት የእኔን ማንነት ለኔ ከመፈረጅ "አልፈው እስከነአካቴው እኔነቴን ይለውጡታል?" ብዬ ቅር ተሰኘሁብዎት:: ስለ እኔ ይበልጥ ለማወቅ ከአሻዎት ግን፣ እኔ እንደ ሁሉም ኢትዮጵያውያን፣ ከኀያሉ ሊቀ-ካሕናትና ንጉሠነገሥት ከኢትዮጵ አብራክ የፈለቅኩና የኦሮሞ፣ የአማራ እና የሌሎቹም ኢትዮጵያውያን አባት ከሆነው ከነቢዩ፣ ከካህኑና ከጠቢቡ የጎጃም ንጉሥ ከደሸት (ደሴትም ይባላል) የተገኘሁ ማንነቴን ጠንቅቄ የማውቅ ጅንን የኢትዮጵያ ኦሮሞ ነኝ:: እንደኔ ዐይነት የሆኑ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ኢትዮጵያውያን እንደ አሉም አያጠያይቅም:: እርስዎ በዲሞክራሲና በሰው ልጅ የመኖር መብት በእውነት የሚያምኑ ከሆነ የዚህ ዓይነቶችም ኦሮሞ ኢትዮጵያውያን መኖራቸውን ተቀብለው በሃገራቸው ላይ እንዲኖሩና ሃሳባቸውንም ያለ አንዳች ፍርሃት በነጻነት ለመግለጽ የሚያስችላቸውን ሰብአዊ-ሃርነት እንደማይነፍጓቸው አምናለሁ:: እንደነዚህ ዐይነቶቹንም ኦሮሞዎች፣ "ትክክለኛውና የጠራሁት ኦሮሞ እኔ ብቻ ነኝና እናንተ ኦሮሞ አይደላችሁም:" ይሏቸዋል ብዬ አላስብም:: ሰው "እኔ ነኝ" የሚለውን ሁሉ የመሆን መብት አለው:: እርስዎ "ኢትዮጵያዊ አይደለሁም፣" የማለት መብት እንደ አለዎት ሁሉ ማለት ነው:: "ኢትዮጵ" የተባለ ታላቅ ሰው አንድ ጊዜ ገንኖ በዚች ዓለም ላይ ስለመኖሩ ግን ማስረጃው ምንድን ነው ከአሉኝ፣ እሩቅ ሳልሄድ ማስረጃውን አቀርብልዎታለሁ:: ማስረጃውም፣ በድሮ ጊዜ መላው አፍሪካ በኢትዮጵ ስም "ኢትዮጵያ" መባሉ (ከ 300 ዓመታት በፊት ፈረንጆች የሳሉትን የአፍሪካ ካርታ ፈልገው ይመልከቱ፤) እና ሲል ሲል ያ ሁሉ ተቀንሶ፣ እንደጥንቱ ትልቅ ባትሆንም ዛሬም "ኢትዮጵያ" የምትባል ሃገርና "ኢትዮጵያውያን" የሚባሉ ሰዎች መኖራቸው ነው:: አለዛ "ኢትዮጵያ" የተባለችው ሃገር በምን የተሰየመች ይመስልዎታል?

እርስዎ የእኔን ማንንት ከመለወጠም በላይ፣ እኔ ስሜን "ቶላሳ" ብዬ ሳልጽፍ ጽፈሃል አሉኝ:: በህጻንነቴ ትምህርት ቤት ስመዘገብ ስሜ በስህተት ወይም ሆነ ተብሎ የአባቴ ስም "ቶሎሳ" ተሰኝቶ ተጽፎ ነበርና ከትምህርት ቤት ጀምሮ እስከዛሬ ይህን ስም በየሰነዱ ላይ ተሸክሜው እዞራለሁ:: አጠራሩን "ቶለሳ" ብሎ ለማስተካከል በተለያዩ ዘመናት በልቤ ባስብም ስሙን ለማስቀየር ህጋዊ ውጣ ውረድ ስለአለው በፓስፖርቴ፤ በዲፕሎማዬ፣ በመንጃ ፍቃዴና በሌሎች ሰነዶቼ ሁሉ ላይ ይሄው ስም ሰፍሮ ይኖራል:: በኢትዮጵያውን የመገናኛ አውታሮች ላይ ግን በቀላሉ እንዳላስተካክለው የሚያግደኝ ነገር ስለሌለ "ቶለሳ" እያልኩ አስተካክዬዋለሁ:: አባቴም አያቴም ኦሮሞ መሆናቸውን አንዳንድ ሰዎች መጠየቅ ስለ አመጡ ደግሞ የአያቴንም ጨመርኩበት::እርስዎ ግን እኔ ልብ ውስጥ የሚኖሩና በኔ እና እንደስማቸው ሰወለጋ ጀግና እና የተከበሩ በነበሩት በ ውድ አያቴ በ ጂግሳ መሃል ያለንን የፍቅር ልክ እሳቸው ወይም እኔ የገለጥኩልዎት ይመስል ለአያቴ ግድ እንደሌለኝ አድርገው በዘለፋ ጻፉብኝ:: የአያቴን ስም ግን ያሰፈርኩት በመጀመሪያ ለእርስዎ በ ከተብኩልዎት ደብዳቤ ላይ ሳይሆን ከሱ ቀደም ብዬ ባለፉት ጥቂት ዐመታት በውይይት መድረኮች ላይና በቅርቡ በፈጠርኳቸው ግጥሞቼ ነው:: አሁንም ቢሆን "ፍቅሬ ቶሎሳ" የተሰኘው ስሜ በዓለም-አቀፍ የደራስያን ሰነዶችና <u>ኤንሲክሎፒዲያ ኦፍ አፍሪካን ሊትሬቸር</u> በተባለው መጽሃፍ ውስጥ ስለገባ እና ከታዋቂ የአውሮፓና የአሜሪካ ደራስያን ስሞች ጋራ በተለያዩ መድበሎች ውስጥ ስለ አለ በዚሁ ስም ታውቄአለሁና፣ አሁን ልቀይረው ስለማልችል ለወደፊት በማወጣቸው መጣጥፎችና መጻሕፍት የተለመደውን "ፍቅሬ ቶሎሣ" ን ማስፈሬ አይቀሬ ነው:: በ እኔ በኩል "ፍቅሬ ቶለሳ ጂግሳ" የተባለው ስም ለኦሮሞና ለአማራው፣ እንዲሁም ለሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ዘመዶቻችን የሚጠቅም የፍቅር ድልድይ ከሆነ "እሰየው! ይበል!" እላለሁ:: ስምን ለሕዝቦች ፍቅር፣ ሠላም፣ ኅብረትና ብልፅግና ማዋል የተቀደሰ ተግባር ነውና:: ከዚህ በተረፈ ግን ስሜ ላይ ማተኮር ምንም ፋይዳ የለውም:: በዚህ ረገድ ፋይዳው መልእክቱ እንጂ መልእክተኛው አደለም:: ስለዚህ እኔን ችላ ብለው፣ በግልጽ ደብዳቤዬ ላይ በሰደድኩልዎት መልእክት ላይ ቢያተኩሩልኝ ደስ ይለኛል::

"ቶሎሳ" የተባለው ቃል ቢያንስ በወለጋ እና ሸዋ ኦሮምኛ ርስዎ እንዳሉት "ቶላሳ" ሳይሆን እኔ ከርስዎ በላይ ባላውቅም "ቶለሳ" ነው:: ትርጉሙም "ቸርነቱ" (የእግዚአብሕር?) ወይም "ደግነቱ" እንደማለት ነው:: ከተሳሳትኩ እታረማለሁ:: እውነቱ ግን፣ እዚህ ላይ እኔ ሳልሆን

እርስዎ የተሳሳቱ ይመስለኛል:: “ቶሎሳ” የተሰኘው ቃል በትክክል ያልተከተበ የኦሮምኛ ቃል እንጂ እርስዎ በግድ ፈጥረው ሊያደርጉት እንደጣሩት “ቶሎ” ከተሰኘው የአማርኛ ቃል ጋር: ምንም ዐይነት ግንኙነት የለውም::  “ቶሎሳ ”  ወይም “ፈጥኖሳ” የሚል የአማርኛ ስም የለምና::

ኦሮሞዎች፣ እማሮች እና ሌሎቹም ኢትዮጵያውያን ከኢትዮጵ እና ከ ደሸት ወይም  ከደሴት ስለመውረዳቸው ትንሽ ማስረጃ ለመቆንጠር ያህል፣ ደሸት ወይም ደሴት የዛሬ 3600 ዓመታት አካባቢ ለልጆቹ የሰጣቸው “መንዲ፣ ጂማ፣  መደባይ”፣  እና “ማጂ” የተባሉት ስሞች አሁንም ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ ይነገራሉ:: ከዚህ በተጨማሪም፣ የዛሬ 800 ዐመት በሰሎሞን ሥርወመንግሥት ስም ነግሶ የኦሮሞን መንግሥት የመሰረተው  ተስፋእየሱስ ወይም ይኩኖአምላክ፣ እናቱ የኦሮሞው የአዛዥ ጫላ ልጅ ጊፍቲ መንዲያ እንደነበሩ የታወቀ ነው:: እንግዲህ “መንዲያ” የሚለው ቃል የኦሮሞ መጠሪያ ሆኖአል ማለት ነው:: ይህም ቃል ከኦሮሞዎች፣ ከአማሮች እና ከሌሎቹም ኢትዮጵያውያን አባት ከ ደሸት ወይም ከደሴት ጋር የቀጥታ ዝምድና አለው ማለት ነው:: ደሸት ወም ደሴት ጎጃም (ጎዣም) ላይ በአንድ ወቅት ለመኖሩ  ደግሞ ማስረጃው እሱ የኖረበትን ስፍራ በስሙ እስጠርቶ ያ ስፍራ አሁንም ድረስ ደሴት ተብሎ በጎጃም ጣና ሃይቅ ዙሪያ መኖሩ ነው:: ይህ የሱን ስም የተሸከመው ደሴት በአማርኛ ቋንቋ በውሃ የተከበበን መሬት መግለጫም ሆኖአል::

ይመኑኝ ዶ/ር በያን አሶባ፣ ኦሮሞዎች ሁሉ የኢትዮጵ ልጆች እና ኢትዮጵያውያን ናቸው:: ኦሮሞዎች ኢትዮጵያውያን ካልሆኑ ታዲያ ምን ሊሆኑ ነው? ባዕዳን መጤዎች ሊሆኑ ነውን? “ኦሮሞዎች ባዕዳን መጤዎች ናቸው” የሚሉ ኦሮሞዎች “ኦሮሞዎች በግራኝ አህመድ ጦርነት ጊዜ ከእስያ ፈልሰው በማዳጋስካር አድርገው ኢትዮጵያን የወረሩ ናቸው፣” ከሚሉት የተሳሳቱ ሰዎች ጋራ መስማማታቸው አይደለም ወይ? ኦሮሞዎች ለኢትዮጵያ ባዕዳን ከሆኑ ደግሞ ኦሮሞዎች የሚያነሱት የመብት፣ የነጻነት እና የመሬት የይገባኛል ጥያቀዎች ከቶውኑ እንዴት ሊሆኑ ነው? ነገሮች እየተስተዋሉ ቢሆኑ መልካመ ይመስለኛል:: የታሪካችን ሃቅ እደሚመሰክረው ግን ኦሮሞዎች ኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠሩ የጠሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው::

በዚሁ ደብዳቤዎ ላይ ስለ ከምባታዎች፣ ሃዲያዎች፣ ወላኢታዎች እና ሌሎችም የደቡብ ሕዝቦች ደማቸውን ማፍሰስ እና አጥንታቸውን መከስከስ ጠቅሰው ነበር:: እነሱን ለምን እዚህ ላይ እንደጠቀሷቸው ግልጽ ባይሆንልኝም፣ እነሱ ምንም እንኳን የኦሮሞዎችና የዝርያዎቻቸውን ያህል ኢትዮጵያን ቢያንስ ለ 800 ዓመታት ገዝተው የማስተዳደር ዕድል ባይገጥማቸውም፣ ለአንዲት ደቂቃም እንኳን ኢትዮጵያዊነታቸውን ጥያቄ ውስጥ ያላስገቡና ሃገራቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነው ለመብታቸው የሚታገሉ ቆራጥ ኢትዮጵያውያን ናቸው::

የተወደዱ እና የተከበሩ ዶክተር በያን አሶባ ሆይ!  ስማችንን እየሰነጣጠቅን ተራ ወግ ከምናወጋ ይልቅ እኔ ለርስዎ በጻፍኩት ግልጽ ደበዳቤ ውስጥ ሰለ አካተትኳቸው የኦሮሞውን፣ የአማራውን እና የሌሎቹን ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን የወደፊት ዕጣ ፈንታ በሚጠቅሱት ቁም-ነገሮች ላይ ብንነጋገርና ለሕዝባችን የሚበጀውን መፍትሄ ብንመካከር በወደድኩ ነበር:: ሆኖም እርስዎ እንደአሉት አዲስ የተቋቋመው የእርስዎ የኦሮሞ ዲሞክራቲክ ግንባር ለኦሮሞውችና ለሌሎቹም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁሉ የሚጠቅመውን መልካም ምላሽ እንደሚሰጥ ተስፋ አደርጋለሁ:: አያሌ ኢትዮጵያውያን መልሱን እየተጠባበቁ ነውና::

የሁሉም ነገር የመጀመርያ መፍትሄ፣ ስለአለፈው ግጭቶችና በደሎች ደጋግመው እያሰቡ ቂም ይዞ ከመራራቅ ይልቅ፣ ተቀራርቦ  “ሰለ ፍቅር፣ በስመአብ ይቅር፣” ተባብሎ ታርቆ፣ ማንም ከማንም በላይ ያልሆነባትን፣ ሁሉም እኩል የሆነባትን የፍትህ፣ የነጻነትና የሰላም አገር አብሮ መገንባት ይመስለኛል:: ቀድሞ ተለያይተው ተራርቀው ይኖሩ የነበሩት አውሮፓውያን እንኳ የተባበሩትን አውሮፓ በኅብረት ፈጥረው በ ኢኮኖሚ እና በፖለቲካ ወደፊት እየገሰገሱ ነው:: እዚህ ላይ  በብልሁና በአርቆ እስተዋዩ በኔልሰን ማንዴላ በ ደቡብ አሪካ የተከናወነውን ዕርቅ መዘከር ይገባል:: እንኳን እኛ በአንድ ምድር የተፈጠርን

**ቀድሞውንም ምንጫችን አንድ ከመሆኑም በላይ እንደገና  ተጋብተን ተዋልደን አንድ ደም እና አንድ አጥንት የሆንን፣ መልካችን እና ባሕላችን የተመሳሰለና የተዋሃደ ወንድማማቾችና እህትማማቾቹ ቀርተን፣ በግፈኞች ነጮች እስር ቤት ለዓመታት የቁም-ስቅላቸውን እየአዩ የማቀቁት ኔልሰን ማንዴላ፣ በጥቁርና  በነጮች መሃል እርቅ ይውረድ ብለው፣ የይቅርታን መንፈስ አግዝፈው ደቡብ አፍሪካን ከቂም-በቀል የደም መፍሰስ እና ከመፈራረስ አድነዋታል።**

**የእኔን እና የእርስዎን ስሞች አስመልክቶ እርስዎ ከዚህ በላይ ለመነጋገር እንደ እማይፈልጉ ሁሉ፣ እርስዎ ሌላ መልስ እስከ አልሰጡኝ ድረስ እኔም በዚህ ዐይነቱ ፋይዳ-ቢስ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር አልፈቅድም። ስለ ሃገራችንና ሕዝባችን ጉዳይ ግን፣ ስሜተኛ ሳንሆን በታላላቅ ኦሮሞዎችና ኢትዮጵያውያን ጨዋነት፣ በሰከነ አእምሮ፣ ብሎም በቀና ልቦና እንወያይ ከአሉ ግን ግብዣዎን ለመቀበል ዝግጁ ነኝ።**

**በመጨረሻም፤ እርስዎ እና ባልደረባዎችዎ ያሰባችሁት ቅዱስ ሃስብ እንዲሳካላችሁ ከልቤ እንደምተጋላችሁ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ። እኔ ቀድሞውንም ያንን ግልጽ ደብዳቤ የጻፍኩላችሁ፣ ለሕዝባችን መፍትሄ የሚሆን የተቀደሰ አዲስ ሃሳብ ይዛችሁ ስለመጣችሁ "እሰየው! ደግ አደረጋችሁ!" ብዬ በቀና መንፈስ  ነበር። አሁንም ቢሆን "በእምትችለው ሁሉ ተባበረን፣" ብላችሁ ከጋበዛችሁኝ ለዚህ የተቀደሰ አላማችሁ አብሬአችሁ ለመሰለፍ ዝግጁ ነኝ።**

## ፍቅሬ ቶለሳ ጂግሳ (ዶ/ር)

***የእግርጌ መግለጫ***-- *ለ አዲሱ የኦሮሞ ዲሞክራቲክ ግንባር መፈጠር ድጋፍ ለመለገስና ለሕዝባችን ይጠቅማሉ ያልኳቸውን የ ግሌን ሃሳቦች ለመግለጽ፣ ባለፈው ጊዜ ለ ዶ/ር በያን አሶባ የጻፍኩት ግልጽ ደብዳቤ እኔ ባላሰብኩት ሁኔታ እንደ ቋያ እሳት ነድዶ፣ በኢትዮጵያ ሳይቀር አያሌ ውይይቶችን ከፍቷል። ይህን አስመልክቶ ብዙ መልካም አስተያየቶች ከበሰሉ ኦሮሞዎች፣ አማሮች፣ ትግሬዎች፣ ሃዲያዎች፣ ከምባቶች፣ ጋምቤላዎች፣ ሱማሌዎችና ሌሎችም በርካታ ኢትዮጵያውያን ከዓለም ዙሪያ ደርሰውኛል። የተቻለኝን ያህል መልስ ሰጥቻለሁ። አኔን በመስደብና ያለ ስሜ ስም በመስጠት ፍሬ-ቢስ ወይም እንቶፈንቶ ነገሮችን ጫጭረዋል። ለሁሉም መልስ ለመስጠት ጊዜና አቅም እንደሌለኝ በዚህ አጋጣሚ ልገልጽ እፈቅዳለሁ። እንደወንጀለኛ ስማቸውን ደብቀው ክብሪት ለሚጭሩት ደግሞ ምንም መልስ የለኝም።  እኔ የማውቀውን እውነተኛውን የኦሮሞ እና የሌሎቹን ኢትዮጵያውያን ታሪክ በቀና መንፈስ ከልቡ ለመረዳት ለሚጓጓ ሁሉ ግን፣ አቅሜ በፈቀደ መጠን ታሪኩን ለማጋራት ምን ጊዜም ወደ ኋላ እንደማልል ለማረጋገጥ እወዳለሁ።*

*ከዚህ በተጨማሪ፣ ኦሮሞ እና አማራ ያልሆናችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ፣ የእናንተም የዘር አባታችሁ ኩሻዊው ኢዮጵ ነው። ከ ዛሬ 4000 ዐመታት በፊት እሱ እናታችንን እንቁዮጳን አግብቶ ዐስር ወንዶች እና ሶስት ሴቶች ልጆች ወልዶ ነበር። የወንዶች ልጆቹ ስም፣ "አቲባ፣ ቢኦር፣ ቢኦራ፣ ተምና፣ ኤቴር፣ አሻን፣ መሪሳ፣ ቴስቢ፣ ቶላ (የኔ አጎት ስም)፣ እና አዜብ"  ናቸው።  የሴቶቹ ደግሞ "ሱባ፣ ሚልካ እና ሎዛ" ናቸው። እነዚህም የታላቁ ኢትዮጵ ልጆች፣ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩትን እጅግ በርካታ ጎሳዎች፣ ነገዶች፣ ብሄሮች እና ብሐረሰቦች ሆነዋል።  በእርግጥም አሁን የአሉት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁሉ ከእነዚስ ሰዎች አብራክ የፈለቁ ናቸው። ስለዚህ ሁላችንም ቤተዘመዳሞች ነን።  ለወደፊቱ፣ ዝርዝሩ እና ምንጩ ይፋ ይሆናሉ።።*

*ፍቅሬ ቶለሳ ጂግሳ (ዶ/ር)*

*እኤአ 06/01/2013*